የወ/መ/ቁጥር 160409

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሰኔ 17 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፣ ወ/ሮ ፈትያ ቢረዳ አብዶ - ቀረበች

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ነሐሴ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በተሻፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሽ በ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሰው አካልና ጤና ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ ታህሳስ 09 ቀን 2001 ዓ.ም በግምት ከጠዋቱ 4፡45 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/05 ልዩ ቦታው አለም ባንክ አደባባይ 84 ማህበር አካባቢ የግል ተበዳይ አበባ ገ/ማርያምን በቆርቆሮ አፍንጫዋን መትታ በማድማቷ በፈፀመችው ቀላል የአካል ጉዳት ማድረስ ወንጀል ተከሳለች በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሽ ደርሷትና ተነቦላት ከተረዳችው በኋላ ክሱን ሳትቃወም፤ ድርጊቱን አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም ብላ ክዳ በመከራከሯ ዐ/ሕግ የግል ተበዳይንና ባለቤታቸውን አቅርቦ ያሰማ ሲሆን እነዚህ ምስክሮችም በክሱ ላይ በተመለከተው ቀን፤ ጊዜና ቦታ በአጥር ምክንያት የግል ተበዳይና ተከሳሽ ሲነጋገሩ ቆይተው በመጨረሻ የግል ተበዳይ ቆርቆሮ አንስታ የግል ተበዳይን አፍንጫ ያደማቻት መሆኑን በማስረዳታቸው ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር እንድትከላከል በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዛለች።

ተከሳሽም እከላከላለሁ ብላ ሁለት የመከላከያ ምስክሮችን አቅርባ ያሰማ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገበችው በወቅቱ እኔ ቤቴ ውስጥ ተኝቼ እያለ ጩኸት ሰምቼ ስወጣ የግል ተበዳይ ደምታ አይቻለሁ፤ እኔ ከመውጣቴ በፊት የእኔ ልጅ ከግል ተበዳይ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤ በወቅቱ አጥር ላይ የነበረን ቆርቆሮ ስታነሳ ነው የተቆረጠችው፤ ይህንም ከመከላከያ ምስክሮቹ ነው ያረጋገጥኩት በማለት አስመዝግባ ምስክሮቹም ቀርበው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበችው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባትን ክስና ማስረጃ አስተባብላለች ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሽ ሁለቱ የመከላከያ ምስክሮች በተከሳሽ ቤት ውስጥ ያለን የፀጉር ቤት ተከራይተው ይኖሩ እንደነበር፤ በታህሳስ 09 ቀን 2001 ዓ.ም ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት እስከ 5፡00 ሰዓት ባለው ጊዜ የግል ተበዳይና የተከሳሽ ልጅ ይነጋገሩ ነበር፤ ወዲያው ደግሞ የግል ተበዳይ ፊታቸው ላይ ወደ አፍንጫቸው አካባቢ ደምተው አይተናል፤ ተከሳሽ ተኝታ ስለነበር በኋላ ነው የወጣችው በማለት መስክረዋል። ይሁን እንጅ ተከሳሽ

በወቅቱ ቤት ውስጥ ተኝታ ከነበር በምን ምክንያት ወጣች የሚለው እና የግል ተበዳይ አፍንጫቸው ላይ በምን ሁኔታ እንደደሙ ምስክሮቹ በቦታው ከነበሩ ለምን ማስረዳት ተሳናቸው። የግል ተበዳይ ቆርቆሮውን አንስተው አፍንጫቸውን በራሳቸው እጅ ቆረጡት የሚባልም አይደለም። የመከላከያ ምስክሮቹ በተከሳሽ ቤት ተከራይተው ስለሚኖሩ ተከሳሽን ነፃ ለማውጣት የሰጡት የምስክርነት ቃል ነው ከሚባል በስተቀር እምነት የሚጣልበት ሆኖ አልተገኘም። ስለሆነም ተከሳሽ ባቀረበችው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባትን ክስና ማስረጃ ለማስተባብል ስላልቻለች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ስር ጥፋተኛ ናት በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የቅጣት ማክበጃም ሆነ ማቅለያ የለንም፤ ነገር ግን ፍ/ቤቱ በሕገ መንግስቱ
አንቀፅ 36(2) ላይ የተደነገገውን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይወሰን
በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 38 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 8 ኛ ክፍል ነው፤ ትዳር
አለኝ፤ መተዳደሪያ ሥራዬ በባለቤቴ ገቢ ነው፤ አራት ልጆች ያሉኝ
ሲሆን ሁለቱ 16 ዓመት እና 8 ወር እድሜ ያላቸው ናቸው፤ ከአሁን ወዲያ
እንዲህ አይነት ድርጊት ላለመፈፀም ቃል እገባለሁ በማለት አመለከተች።

ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትህዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ጥፋተኛ የተባሉበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 556(2)(ሀ) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 2 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 5 ነው። ስለሆነም የዚህ እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጥን/range/ ከስድስት ወር እስከ ዘጠኝ ወር ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ የወሰነው መነሻ ቅጣት ሰባት ወር ከአስራ አምስት ቀን ቀላል እስራት ነው።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84 ወይም 85 መሰረት የቅጣት ማክበጃ ያላቀረበ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የመነሻውን ቅጣት እርከኑን ከፍ ሳያደርግ እንዳለ እርከን 5 ን ወስዶታል።

ተከሳሽ በበኩላቸው የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 እና 86 ላይ በተመለከቱት መሰረት በማስረጃ የተደገፉ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች አላቀረቡም፤ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የቅጣቱን እርከን ዝቅ አላደረገውም።

ስለሆም በማክበጃ ምክንያቱ መሰረት ከፍ ያለ እና በማቅለያ ምክንያትም ዝቅ ያለ ስለሆነ ከላይ በተወሰነው መሰረት ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በሰባት ወር ከአስራ አምስት ቀን ቀላል እስራት እንድትቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ በአሁኑ ወቅት ሁለት አካለመጠን ያላደረሱ ልጆች እናት ስለመሆኗ
ልጆቹ በአካል አቅርባ በማሳየት የተገፀች ስለሆነ፤ ሕፃናት ልጆች
የቤተሰባቸውን የቅርብ ክትትልና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው በሕገ
መንግስቱ አንቀፅ 36(1) (ሐ) ላይ የተደነገገ ስለሆነ፤ ለሕፃናት ልጆች ሲባል
የእስራት ቅጣቱ ከሚፈፀም ይልቅ ለተከሳሽ አንድ ዕኑ ማስጠንቀቂያ
ተሰጥቷት ፀባይና አመሏ ወደፊት ቢታይ መልካም ስለሆነ የእስራት ቅጣቱን
በወንጀል ሕግ አንቀፅ 192 መሰረት በሦስት ዓመት ገደብ አግዶታል።

2 ኛ. ተከሳሽ ለመልካም ፀባይ አመራር ዋስትና ይሆን ዘንድ ለብር
500.00(አምስት መቶ ብር) የሚበቃ ዋስትና ትጥራ።

3 ኛ. ተከሳሽ ለፅህፈት ወጪ ብር 25.00(ሃያ አምስት ብር) ለመንግስት ትክፈል።

4 ኛ. ተከሳሽ የፅህፈት ወጪ የተባለውንና የመተማመኛ ዋስትናውን ስትከፍል
ትለቀቅ።

5 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

6 ኛ. በዚህ መዝገብ የተሰጠ የዋስትና ግዴታ ካለ ቀሪ ሆኗል።

7 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

<u>ተጨማሪ ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ ከዛሬ ጀምሮ የሁለት ዓመት ጊዜው እስኪጠናቀቅ ድረስ ከግል ተበዳይ ጋር ወይም ከግል ተበዳይ ቤተሰቦች ጋር ሌላ የወንጀል ድርጊት ብትፈፅም በአካባቢው ያለው የሕግ አስከባሪ ማለትም የክፍሉ የቀበሌ አስተዳደር ወይም የክፍለ ከተማው ፖሊስ መምሪያ በማስረጃ መደገፉን አረጋግጦ ለፍ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርግ ታዟል። ይፃፍ።

2 ኛ. ተከሳሽም ፍ/ቤቱ በዚህ ችሎት የሰጣትን ጥብቅ ማስጠንቀቂያ ታሳቢ በማድረግ መልካም ዜጋ ሆና በሰላም ከጎረቤቶቿ ጋር እንድትኖር ተነግሯታል።

3 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መ/ቤት ይመለስ።